ብርሃኑ በላቸው

# «ቪዛ የተከለከሉ መሪዎቻችንን ቴክኖሎጂ ተጠቅመን አመጣናቸው»

የቅንጅት መሪዎች ወደ ካናዳ እንዳይገቡ ቪዛ ለምን ተከለከሉ? የየካቲት 30 ስብሰባችሁስ እንዴት ነበር? እነዚህንና ሌሎችንም ጥያቄዎች አንስተን በቶሮንቶ ካናዳ ከሚገኘው የቅንጅት ድጋፍ ጽህፈት ቤት ሊቀመንበር ከአቶ ቢሹ ማሞ ጋር አጠር ያለ ቃለመጠይቅ ይዘን ቀርበናል።

## አቶ ቢሹ ማሞ
## በቶሮንቶ ካናዳ የሚገኘው የቅንጅት ድጋፍ ጽህፈት ቤት ሊቀመንበር

ጉግል፡ በቅድሚያ በቶሮንቶ ካናዳ ስለ እናንተ የድጋፍ ድርጅት ቢገልጹልን

አቶ ቢሹ ማሞ፡ የቶሮንቶ ካናዳ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት በካናዳ ሕግና ደንብ መሰረት በሕጋዊነት ተመዝግቦ ለብዙ ዓመታት ሲንቀሳቀስ የቆየ ሲሆን ቅንጅት ከመመስረቱ በፊትም የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የድጋፍ አካል ሆኖ በአገራችን እየተካሄደ ያለውን የዲሞክራሲ ትግል በሚቻለው አቅምና መንገድ ሁሉ ሲረዳ ነበር። በመቀጠልም ለምርጫ 97 ሲቃረብና ቅንጅት እንደተመሰረተ የቅንጅትን መንፈስና ዓላማ በመከተል የቅንጅት ድጋፍ አካል ሆኖ ለምርጫው የሚረዳ አስተዋጽኦና የሞራል ድጋፍ ሲሰጥ የቆየ ድርጅት ነው። በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ስለ አገሩ የፖለቲካ ሁኔታ ትክክለኛ መረጃ ከትግሉ ቦታና ከታጋዮቹ በመስማት በካናዳ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዜናዎችን ሲያሰራጭና ሲቀሰቅስ ስለ ወቅቱ የአገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሲያስተምር ቆይቷል። የወገኖቹን ስቃይ፣ መከራና ችግርም ሲያስተጋባ እናም አብሮ ሲጮኽ ቆይቷል።

ጉግል፡ የቅንጅት ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልና የሚመሩት የልዑካን ቡድን በቅርቡ ወደ ካናዳ ለመምጣት ቪዛ ጠይቀው ተከለከሉ ይባላል እውነት ነው? ስለእርሱ ቢያስረዱን?

አቶ ቢሹ ማሞ፡ ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የቅንጅት ፕሬዚዳንት በአሜሪካ የሚያደርጉትን የሥራ ጉብኝት በመቀጠል በቶሮንቶም ካናዳ ተመሳሳይ የሥራ ጉብኝት እንዲያደርጉ፣ ቃሊቲ በታሰሩበት ጊዜ ድምጹን ሲያሰማና ሲጮኽ ለነበረው ሕብረተሰብ ምስጋና ለማቅረብና ለወደፊቱም የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ውይይት ለማድረግ በማቀድ፣ እርሳቸው የሚመሩት የልዑካን ቡድን ማለትም የቅንጅት የላዕላይ ምክር ቤት አባል የሆኑትን ወይዘሮ ንግሥት ገብረሕይወት እና አቶ ማሙሸት አማረን እንዲሁም በአሜሪካ ነዋሪ የሆኑትን የቅንጅት ዓለም አቀፍ ምክር ቤት ሊቀመንበር ዶክተር ታዬ ወልደሰማያትን ወደ ቶሮንቶ እንዲመጡ የጥሪ ደብዳቤ ልከን ነበር። የአቶ ማሙሸት አማረ የቪዛ ማመልከቻ አዲስ አበባ ካናዳ ኤምባሲ አመልክተው ቪዛው ከናይሮቢ ስለሚሰጥ ፓስፖርታቸው ከተላከ ከስድስት ወር በላይ ሆኖታል። ፓስፖርታቸው እንዲመለስ ካመለከቱ አንድ ወር ቢሆናቸውም እስከ ዛሬ ድረስ ግን አልመለሱላቸውም።

አቶ ማሙሸት የቪዛ ጥያቄ ያቀረቡት ሁለት ጊዜ ቀደም ብሎ ከ6 ወር በፊት ከእነ አቶ ደበበ እሸቱ ጋር አመልክተው የአቶ ደበበ ሲፈቀድ የሳቸው መልስ አጥቷል።

ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት ያቀረቡት የቪዛ ማመልከቻ ዋሽንግተን ዲሲ ያለው የካናዳ ኤምባሲ 10 ደቂቃ ባልሞላው ጊዜ ውስጥ "አንተ ካናዳ ገብተህ ስለምትቀር ቪዛ አንሰጥህም" ተብለው ሲከለከሉ ማመን ያዳግታል። ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት ወደ ካናዳ ከአንድም ሁለት ሶስቴ ገብተው የወጡ እና በአሜሪካ ቺካጎ በሚገኝ ዩንቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስ ፕሮፌሰር ሆነው እየሰሩና ከዩንቨርስቲው የሥራ ደብዳቤ አቅርበው እያለ ቪዛ መከልከላቸው ጉዳዩ ሌላ እንደሆነ ለማወቅ ብዙም መጠየቅ አያሻውም።

ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል እና ባለቤታቸው እንዲሁም የቅንጅት የላዕላይ ምክር ቤት አባል የሆኑት ወይዘሮ ንግሥት ገብረሕይወትም ዋሽንግተን ዲሲ ላለው የካናዳ ኤምባሲ የተላከላቸውን የጥሪ ደብዳቤ፣ የአየር ቲኬትና የሚሄዱበትን ጉዳይና ቀን ጠቅሰው አስፈላጊውን የማመልከቻ ቅጽ ሞልተውና ከፍያ አድርገው ለካናዳ ኤምባሲ አመለከቱ። ተደርጎ የማይታወቅ ነገር ወደ ሶስት ሳምንት ገደማ ቪዛ ሳይሰጧቸው በመዘግየቱ ቀደም ብሎ የተያዘው የቶሮንቶ ሕዝባዊ ስብሰባ ፕሮግራም ከየካቲት 16 ወደ የካቲት 30 እንዲተላለፍ ተደርጎ ቢጠበቅም ለእነኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ብቻ "ቪዛ ከኦታዋ እየተጠበቀ ነው" በማለት በካናዳ ኤምባሲ የማዘግየት ሴራ ተፈጽሞባቸዋል። የተፈለገው ነገር ቢኖር ካናዳ ካሉ ኢትዮጵያኖች ጋር ግንኙነት እንዳያደርጉ ለማድረግ ነው። በአንጻሩ ግን በመጀመሪያ ማመልከቻ ብቻ ለእነ አቶ ደበበ እሸቱ ቪዛ ተሰጥቶ አቶ ማሙሸት አማረ ለምን ተከለከሉ? ለወይዘሮ ብርቱካን ሚደቅሳ ቪዛ ተሰጥቶ ለክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ለምን ተከለከለ? እነ ልደቱ አያሌው እና እነ ዶክተር በየነ ጴጥሮስ ሲሰጣቸውና ካናዳ ተዝናንተው ሲመለሱ ለእነ ወይዘሮ ንግሥት ለምን ተከለከሉ? መልሱ ግልጽ ነው።

እውነተኛ የሕዝብ ወገኖች፣ ሐቀኛ ኢትዮጵያውያን ከሕዝብ ጋር እንዳይገናኙ ለማድረግ ከወያኔ ጋር በማበር የተፈጸመ ደባ ነው። ድርጊቱ የአንድነት ኃይሎችን ለማዳከምና የፀረ–አንድነት ቡድኖችን ለማጠናከር የተደረገ ሴራ ነው።

Canada-Toronto, Kinijit Task Force, March 22, 2008

ጉግል፡ በእናንተ በኩልስ ምን ያደረጋችሁት ጥረት አለ በካናዳ መንግሥት በኩል ቪዛ እንዲሰጣቸው?

አቶ ቢሹ ማሞ፡ በእኛ በኩል አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ያሟላን ከመሆኑም ሌላ ኢምባሲውንና ከፍተኛ ባለሥልጣኖችን በማነጋገር ቪዛ እንዲሰጣቸው ብዙ ጥረት አድርገን እንደሚሰጣቸውም ቃል ገብተውልን ነበር። ዋሽንግተን ዲሲ የመንግሥት ሥራ ላይ ባሉ ካናዳዊ አማካኝነት ብዙ ጥረት ተደርጎ የራሳቸውን ዜጋ እንኳን በሚያሳፍር መልኩ መልስ አልተሰጠም። የካናዳ ከፍተኛ ባለሥልጣን ዘንድ ጉዳዩን ለማቅረብ ተችሎ ቪዛ እንደሚሰጣቸው ቃል ከገቡና ተስፋ ከሰጡ በኋላ የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቷል። ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት ቪዛ እንደተከለከሉ ሲቀር የሌሎቹ ቪዛ ደግሞ ምንም ዓይነት ምላሽ ሳያገኝ የታቀደው የሥራ ጉብኝት ፕሮግራም ቀን ተራዝሞም እንኳን ባለማግኘታቸው ሊመጡ አልቻሉም።

ጉግል፡ ሁለተኛው የታቀደው ስብሰባስ ባለመምጣታቸው ተሰረዘ ?

አቶ ቢሹ ማሞ፡ አልተሰረዘም። በእኛ በኩል ወደ ካናዳ የሚመጡበት እለት እኩለ ቀን ድረስ ተጠብቆ በማግሥቱም ቅዳሜ በመሆኑና ኢምባሲው ዝግ በመሆኑ መምጣት እንደማይችሉ ስናውቅ ሌላ አማራጭ መንገድ ፈለግን እና እቅዳችን ተሳክቶ የታቀደው ሕዝባዊ ስብሰባ ተካሄደ።

ጉግል፡ ምን ነበር ሌላው አማራጭ?

አቶ ቢሹ ማሞ፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የተፈለገው የእነ ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የልዑካን ቡድን ወደ ካናዳ እንዳይመጣ የተለያዩ መሰናክሎችን በመፍጠር ከኢትዮጵያኖች ጋር እንዳይገናኙ ማድረግ ነበር። ሆኖም ግን የነን የፈለጉ ኃይሎች አልተሳካላቸውም። ባለን ሌላ አማራጭ ተጠቅመን ስብሰባው ተካሄደ። በአሜሪካ ያሉ ታታሪ ወገኖቻችንና ቶሮንቶ ካናዳ ያሉት በመተባበር በዘመኑ ቴክኖሎጂ ተጠቅመን የታቀደው ሕዝባዊ ስብሰባ በተሳካ እና በደመቀ ሁኔታ ሊካሄድ ችሏል። ይኸውም ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልና ወይዘሮ ንግሥት ገብረሕይወት በቪዲዮ ኮንፈረንስ ከዋሽንግተን ዲሲ፣ ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ እና አቶ ማሙሸት አማረ ከአዲስ አበባ፣ ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት ከቺካጎ በጋልቶክ አማካኝነት ሊሳተፉ ችለዋል። ሕያው የቪዲዮ ኮንፈረንሱ ሁለቱ ከተሞች ማለትም ዋሽንግተን ዲሲ ያሉት የቅንጅት መሪዎችና ቶሮንቶ በአዳራሽ ያለው ሕዝብ እየተያየ ስብሰባው ተካሄደ፣ ውይይቱ ቀጠለ ጥያቄና መልስ ተደረገ። የከለከሉትን ቪዛ በራሳቸው ቴክኖሎጂ ተጠቅመን መሪዎቻችንን አመጣናቸው። ይህን ዓይነት ሕዝባዊ ስብሰባም ሲካሄድ ይህ የመጀመሪያው መሆኑ ነው። በእውነቱ እጅግ መሳጭና ከፍተኛ የደስታ ስሜት በሕዝቡ ዘንድ ይንጸባረቅ ነበር። የአንድነት ኃይሉ ክፍል ሌላ ድል አስመዘገበ።

ጉግል፡ በየካቲት ሰላሳው ቶሮንቶ ባደረጋችሁት ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ የተሰብሳቢውን ቀልብ የሳበ ነገር ካለ ቢገልጹልን?

አቶ ቢሹ ማሞ፡ አዎን በዋሽንግተን ያለትን ልዑካን፣ በአዳራሹ ያለውን ተሰብሳቢ እና በመላው ዓለም በጋልቶክ ክፍል ያለውን ታዳሚ የሳበው ካናዳ ተወልደው ባደጉ ሁለት የ13 ዓመት ታዳጊ ወጣቶች በአማርኛና በእንግሊዝኛ የቀረበው መልዕክት በጣም ልብን የሚነካ ነበር። ወያኔ ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር ያልተወለዱት ልጆች ዛሬ የወያኔ ኢሕአዴግ አገዛዝ በምርጫ 97 ሳቢያ ሕዝቡ ላይ ያካሄደውን ግድያና እስራት ስቃይና መከራ በዜና ማሰራጫዎች በመከታተላቸው እና የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖርበትን የኑሮ ደረጃ፣ በእነርሱ እድሜ ያሉ ታዳጊዎች የሚያሳልፉትን የመከራ ኑሮ እና በአሜሪካና እና በካናዳ ያለው መብት፣ ነጻነትና እድገት በኢትዮጵያ ለምን እንደሌለ በመጠየቅ ለሀገሩ የሚቆረቆር፣ ለሕዝቡ የሚያስብና ሕዝብ የሚወደው መንግሥት ቢመሰረት ችግሩ ሊቃለል እንደሚችል ጠቁመው ያ ሕልማቸውና ፍላጎታቸው እስከሚሳካ ድረስ እንደሚታገሉ ቃል በመግባታቸው ኢትዮጵያዊነት እየለመለመ እንጂ የማይጠፋ መሆኑን ለማረጋገጥ ችለዋል። በአዳራሹ የነበረው ሕዝብ በታዳጊ ወጣቶቹ መልዕክት ልቡ ተነክቶ ሕዝቡ እንባውን ያፈስ ነበር።

እንዲት እናትም በኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ የጥንቷን የኢትዮጵያ ካርታ በጥልፍ ሰርተው "አንድ አገር አንድ ሕዝብ" የሚል ቃልም የተጠለፈበት ለክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በስጦታ አበርክተዋል።

ሌላው አንድ አገር ወዳድ የተቃጣብንን የአገር ማጥፋት ሥራ በዶክመንትነት ያሰባሰቡትን የተለያዩ ሰነዶችና መረጃዎች በቶሮንቶ ድጋፍ ድርጅት በኩል ለክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል እንዲሰጥላቸው አበርክተዋል።

ጉግል፡ ከመሰናበታችን በፊት የሚያስተላልፉት ተጨማሪ መልዕክት ካለ

አቶ ቢሹ ማሞ፡ በእውነቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም፣ ጤንነት፣ ደስታ፣ ብልጽግና እና እድገት አግኝቶ ከበሽታ ከድህነት ከኋላ ቀርነትና ከልመና እንዲላቀቅ ከተፈለገ ለሕዝቡና ለሀገሩ የሚቆረቆር መሪና መልካም አስተዳደር ሊኖረው ይገባል። ያ ደግሞ በቀላሉ የሚሆን ነገር አይደለም ብዙ ትግል ይጠብቀዋል ነገር ግን ተስፋ ሊኖረው ይገባል። ለዚህ ሁሉ በአገር ቤትም በውጭም ዓለም ያሉት ኢትዮጵያውያን በተባበረ ትግል ለመልካም አስተዳደር እና ለነጻነት መታገል ስላለባቸው እኛም በውጭ ያለነው የዚያ ትግል አካል ለመሆን ከምን ጊዜውም በበለጠ ድጋፋችንና አስተዋፅኦአችንን ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን ልገልጽ እወዳለሁ። በቶሮንቶ ካናዳም ሆነ በሌላው አገር ያሉት ኢትዮጵያውያን የተጀመረውን የዲሞክራሲ ትግል ከግቡ ለማድረስ ቆርጠን ተነስተናል። በዚህም እንኮራለን። እግዚአብሔር እንደሚረዳንም አልጠራጠርም።

ጉግል፡ እናመሰግናለሁ ስለሰጡን ቃለመጠይቅና ማብራሪያ

አቶ ቢሹ ማሞ፡- እኔም ይህንን እድል በማግኘቴ በጣም አመሰግናለሁ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

Canada-Toronto, Kinijit Task Force, March 22, 2008